
## የመንበረ ፀባዖት ቅ/ ሥላሴ ካቴድራል በ፲ ዓመት ውስጥ ያሳተማቸው መጻሕፍት ።

፩/ መጽሐፈ ሕግጋት ዐበይት
፪/ ፍትሐ ነገሥት ሙሉ ትርጉም
፫/ የወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜ
፬/ መጽሐፈ ድጓ
፭/ አምስቱ ፀዋትወ ዜማ
፮/ ዜቅ
፯/ ፍትሐ ነገሥት ነጠላ ትርጉም
፰/ መጽሐፈ ቅዳሴ ግእዝና አማርኛው ከነምልክቱ
፱/ መዝገበ ሃይማኖት
፲/ ምሥጢረ ሥላሴ
፲፩/ አቡሻክር
፲፪/ የኢ/ ኦ/ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በእንግሊዝኛ
፲፫/ ፩ኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ
፲፬/ ፪ኛ/ የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ
፲፭/ ፫ኛ/ የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ
፲፮/ ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም
፲፯/ ታላላቅ የምሥጢር ሃይማኖት መሥራቾች
፲፰/ መጽሐፈ ኪዳን
፲፱/ ጽድቀ ሃይማኖት
፳/ መዝሙረ ዳዊት
፳፩/ ትንሣኤ (መጽሐ.ት)
፳፪/ ትንሣኤ ግእዝ

# የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ

# ካቴድራል የ፲ ዓመት



# የሥራ ውጤት

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ


1 መቅድም ፩

2 የመንበረ ፀባዖት ቅ/ ሥላሴ ካ. የ፲ ዓመት የሥራ ውጤት - - - - ፫

3 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት የ፲ ዓመት የሥራ መግለጫ ፲፪

4 የሥላሴ ትምህርት ቤት እንዴት ተጀመረ ? - - - - - - - - - - ፲፬


5 ማኅበረ ክርስቶስ በአሥር ዓመታት ውስጥ - - - - - - - - - - - - ፴


www.ethiopianorthodox.org

# የመንበረ ፀባዖት ቅ. ሥላሴ

# ካቴድራል የ፲ ዓመት

# የሥራ ውጤት



የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልና ት/ ቤቱ ።

ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ. ም.

አዲስ አበባ

በብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት ታተመ ።

## መ ቅ ድ ም ።

የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከፍተኛ ምሳሌነት የሚወሰድ በት ፤ የሥልጣኔ ጮራ የሚወጣበት ካቴድራል በመሆኑ ፤ በርሱ አማካይነት የሚ ፈጸሙት አገልግሎቶች ሁሉ በማነስና በማደግ በአንዳንድ ቦታዎች የሚፈጸሙ ሁነዋል ። ካቴድራልም ከተባለና ከሆነ ይኸንኑ የሥራ ጀማሪነት ፤ የበጎ ምሳሌ ነት ምንጭ መሆን እንዳለበት ሁሉም የሚያምንበትና የሚጠብቀው እውነት ነው ።

ለምሳሌ በሰንበት ት/ ቤት ወጣቶች ወንዶችን ፤ ሴቶችንም በትክክሉ በማሠልጠን ቀዳሚነትን የወሰደ ይኸው ካቴድራል ነው ። ከዚያ በኋላ ግን ብዙ ዎች ምሳሌነቱን በመከተል ይሠራሉ ። ስለዚህም በተለይ ሴቶች ወጣቶች ከፍ ተኛ ማኅበር አቋቁመው ፤ በቀጥር በርክተው ተፈላጊውን አገልግሎት ፈጽመው የማኅበራቸውን አሥረኛ ዓመት ዛሬ ያከብራሉ ።

ካቴድራሉ በሬዲዮ ስብከትና ቋሚ ትምህርት ሲሰጥ የነበረና በመስጠትም ላይ የሚገኝ ነው ። እንዲያውም ለቤተ ክርስቲያናችን ሞገስ የሆነውን ሐዋር ያዊ ድርጅት አቋቁሞ የሚሠራው በዚሁ ምክንያት ነው ። ይኸንም ታላቅ ምሳ ሌነት በመከተል ጥቂቶች ተመሳሳይ እርምጃ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።


ይኸም ሐዋርያዊ ድርጅት በውስጡ የጋዜጣ ፤ የሬዲዮ ስብከትን በመጨ መር የ፲ ዓመት የሥራ ውጤቱን ለማሳየት በዛሬው ዕለት በዓሉን ያከብራል ።

ይኸ ካቴድራል ትምህርት ቤት ከፍቶ ፤ ድርጅቱን አሟልቶ ይሠራል ። ለም ሳሌ የሥላሴ ት/ ቤት ከተጀመረ አንሥቶ ሙሉ ዝግጅት ያለው ሆኖ ሲቀርብ ዛሬ ፲ኛ ዓመቱ ነው ። ት/ ቤቱ የተቋቋመበት ዋናው ዓላማ ፤ የጥንቱ የቅ/ ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ ቤት የ፩ኛውና የ፪ኛው ደረጃ ት/ ቤት ስለተዘጋ ፤ ካህናትን በተ ፈላጊው መልክ ለማሠልጠን እንዲችል ነው ። ት/ ቤቱም በቀላሉ ይጀመር እንጂ እየዋለ ፤ እያደረ ግን ዛሬ ካለበት ከተደናቂነት ደረጃ ደርሶ ይገኛል ። ይኸ ንንም ምሳሌነት ብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት እየተከተሉ ት/ ቤት በመክፈት ፤ ሥርዓተ ትምህርቱን በመከተል መሥራት ጀምረዋል ።

ካቴድራሉ መጻሕፍትን በማስተርጐም ፤ በማሳተም ፤ በገበያም በማዋል ተወ ዳዳሪነት የሌለው ድርጅት ሆኖ ይገኛል ። ዛሬ ሁሉም የሚመለከተውና ለአስረ ጂነት የሚጠቅሰው በካቴድራሉ የታተሙትን በቁጥር በርክተው ፤ በዓይነት ምርጥ የሆኑ መጻሕፍትን ነው ። ካቴድራሉ እኒህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ምሳሌነቱን ገና ሌሎች ያልተከተሏቸው ሥራዎችን ያከናውናል ። የካቴድራሉን የሥራ ውጤት ያልሰሙት እንዲሰሙት ፤ ያላዩት እንዲያዩት በማሰብ በጥቅላላ የ፲ ዓመት የሥራ ውጤቱን በዚህ ጽሑፍ አሰፍሮ ይገኛልና ሁሉንም እንድንመለ ከት ይጋብዛል ።

ክቅ/ ሥላሴ ካቴድራል
የድርሰት ክፍል

www.ethiopianorthodox.org



የክርስትና ሃይማኖት ጠባቂ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ።



www.ethiopianorthodox.org


# የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

## የ፲ ዓመት የሥራ ውጤት

በታላቁ ንጉሠ ነገሥታችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተመሠረተውና የተቋቋመው የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በማንኛውም በኩል ሙሉ ዝግጅት ያለው ሆኖ ጥንታዊውን ሥነ ሥር

፩ኛ፤ ውስጣዊ አገልግሎት ማለት ውዳሴ ውና ቅዳሴው ፤ የማኅሌቱም ሥርዓት በትምህርታቸው ላቅ ብለው በታወቁ ልዑካንና መዘምራን በመከናወኑ ፤

፪ኛ፤ ስብከቱ የዘመኑን ችግር ከነመፍት



መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል (ርእሰ አድባራት ዘኢትዮጵያ)።

ዓት ከዘመናዊ አመራር ጋር አስተባብሮ ይዞ በመገኘቱ ፤ የምእመናንን ሕሊና የሚስብ ፤ ማንኛውንም ጉብኚ የሚማርክ ሆኖ ተገኝቷል ።

ሔው ለይተው በሚያውቁ ሰባክያን በመሰጠቱ ፤

፫ኛ ፤ ጠቅላላው የቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት በመጠበቁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፬ኛ፤የአካባቢው ንጽሕና በሚገባ በመያዙ ሲሆን ፤ ሌላም ይኸን በመሳሰለ ብዙ ምክንያት የከተማው ሕዝብ በብዛት ወደዚህ ካቴድራል ሲጐርፍ ይገኛል ። በንብረት አጠባበቅም በኩል የሒድን እንደሆነ ፤ ካቴድራሉ በቀ. ኃ. ሥ. በጎ አድራጎት ድርጅት ሥር ስለሚተዳደር ደንበኛ ቊጥጥር ይደረግለታል ።

ፈጽሞ ይገኛል ። በጠቅላላም በ፲ ዓመት ውስጥ ያደረገውን ለውጥ በዝርዝር እንመልከት ።

## ፩ኛ ትምህርት ቤት በየቦታው መክፈት ።

« ሑሩ ወመሐሩ» ያለውን ቋሚ ትእዛዝ በመከተልና የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ሥራ ት/ ቤት መክ



የቀ. ኃ. ሥ. በጎ አድራጎት ድ. አስተዳዳሪ አቶ አበበ ከበደና የድርጅቱ ባልደረቦች ካቴድራሉን በጎበኙ ሲጎበኙ ።

ካቴድራሉ እንደ ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን በአጥቢያው ብቻ ሳይወሰን የክፍሉን አገልግሎት በሚገባ ፈጽሞ የቤተ ክህነቱን ሸክም በሚቃለል ሲሠራ ይገኛል ። ካቴድራሉ እንደሌሎቹ ቤተ ክርስቲያናት በውዳሴና በቅዳሴ ብቻ ሳይወሰን ፤ ከዚህ በታች ያሉትን ግዳጆች

ፈት ስለሆነ ፤ ካቴድራሉ ብዙ ት/ቤቶችን ሠርቶ ያስተምራል ።

ሀ/ በካቴድራሉ አካባቢ ከ፩—፲፩ ክፍል ከፍቶ ዘመናዊውን ፤ የሃማኖትንና የግእዝ ትምህርትን በቂ በሆኑ አስተማሪዎች ያስተምራል ። ይኸም ተፈላጊውን አገልግሎት



እየሰጠ ዛሬ ፲ኛ ዓመቱን የሚያከብረው ነው ።

ለ/ በልዩ ልዩ ጠ/ ግዛቶች ከ፩—፮ ክፍል ያላቸው በቊጥር ፩ ትምህርት ቤቶች ከፍቶ ያስተምራል ።

ሐ/ የሰንበት ት/ ቤትን በካቴድራሉ አካባቢና በልዩ ልዩ ቦታ ይሰጣል ። አንድ ቤተ ክርስቲያን ይኸን ያህል ርዳታ ለቤተ ክርስቲያን ሲያበረክት ፤ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በሰበካው በዚህ መልክ ቢሠራ ምን ያህል ቤተ ክርስቲያናችን በደረጀች ? ሃይማኖታችን በተከበረ ነበር ። የሀገር ልማት ፤ የሕዝብ ዕድገትም የሚገኘው በዚህ መልክ ሁሉም የበኩሉን ሲሠራ መሆኑ የታመነ እውነት ነው ።

## ፪ኛ ፤ መጻሕፍት ማሳተም ፤


ካቴድራሉ ከሥራው ከፍተኛ ክፍል አድርጎ የያዘው መጻሕፍትን ማሳተምና ለምእመናን ማዳረስ መሆኑን በመገንዘብ ከፍ ያለ ባጀት ወስኖ በዓይነት ልዩ የሆኑትንና በቊጥር በርከት ያሉትን መጻሕፍት በየጊዜው አሳትሟል። አሁንም በማሳተም ላይ ይገኛል ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ ጥንታውያን የሆኑ የትርጉም መጻሕፍትን ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ሕገ ትምህርት መሠረት ከግእዝ ወደ አማርኛ በመተርጐም ብዙ አሳትሟል ።

ለ/ የዜማ መጻሕፍትን ከነምልክታቸው በቅደም ተከተል በመላ አሳትሟል ።

ሐ/ ለጸሎትና ለልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉትን ብዙ መጻሕፍት አሳትሟል ።

መ/ ለቅዳሴ ፤ ለውዳሴ የሚያስፈልጉትን መጻሕፍት አሳትሟል ።



ካቴድራሉ ያሳተማቸው መጻሕፍት ።

www.ethiopianorthodox.org

ሠ/ ለትምህርትና ለተግሣጽ የሚሆኑ ትን ደረጃ በደረጃ አሳትሟል ።

በዚህ በ፲ኛው ዓመት የካቴድራሉ የሥራ ውጤት መጻሕፍትም በኤግዚቢሽን ይቀርባሉ ።

## ፫ኛ ፤ ሐዋርያዊ ድርጅትን ማቋቋም ፤

ለአሁኑ ለኛ ዘመን ሐዋርያዊ ተግባርን መፈጸም ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በጣም አስፈላጊ ነው ። ስለዚህም ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከመንፈሳዊ ቅናታቸው የተነሣ ሐዋርያዊ ድርጅትን አቋቁመው በካቴድራሉ ሥር እንዲተዳደር አደረጉ ። ሐዋርያዊ ድርጅታችንም በጣም አስፈላጊ መሆኑን ፤ በቂ ድርጅት ያለው አድርገን ስናካሒድ ይኸው ፲ኛ ዓመቱን ዛሬ ያከብራል ። ይኸም ሐዋርያዊ ድርጅት ፤ —

ሀ/ እንደ ጎብስት ጣዕም ያለውን የማያቋርጥ ስብከትን በየዕለቱ በሬዲዮ ፤ በትምህርት ቤት ፤ በእሥር ቤት ፤ በሌላም በልዩ ልዩ ቦታ የሚሰጡ ሰባኪዎችን አሰልፎ ያሠራል ።

ለ/ ልዩ ልዩ መግለጫዎችን ፤ ጋዜጦችን በየጊዜው ያሳትማል ። በሥነ ጽሑፍም በኩል ያደረገው እርምጃ ከፍ ያለ ስለሆነ ፤ ፲ኛ ዓመቱን ያከብራል ።


ሐ/ ዘመን አመጣሽ ወረርሽኝ ( የወጣት አጥፊዎችን ) ለመለወጥና የተናወጠውን የሥነ ምግባር ትምርት ፤ ወደቀደመ ቦታው ለመመለስ ብዙ ጥረትን ያደርጋል ። በጠቅላላውም የተሰበረውን የሰው ልጅ ልቡና ለመጠገን ከፍ ያለ ጥረትን ያደርጋል ።

## ፬ኛ ፤ የልማት ሥራን ማከናወን

ማንኛውም ሥራ በእግዚአብሔር የተፈቀደ ቅዱስም መሆኑን ቤተ ክርስቲያናችን ማስተማር አለባት ። እንዲሁም ማስተማር ብቻ ሳይበቃ ሠርቶ ማሳየትም የቤተ ክርስቲያን ተግባር ነው ። ስለዚህ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከሌላው ሐዋርያዊ ተግባሩ ጋር አጣምሮ ፤ በልማት ሥራ ተሠማርቶ ሲሠራ ብዙ ጊዜው ነው ፤ ይኸውም ፤ —

ሀ/ አሩሲ አርባ ጉጉ ፣ አዋሽ ደብረ ፀሐይ ኪዳነ ምሕረት በሚባሉት ርስቶች ላይ የእርሻንና የከብት ማርባትን ሥራ በማካሔድ ላይ ይገኛል ።


ለ/ የሥጋጃ ሥራን ከሁሉ ፤ በበለጠ አስፋፍቶ ይሠራል ። በዚህም እስከ መቶ የሚደርሱ ሠራተኞችን አስተዳድሮ የሙኖሪያ ዘዴ ፈጥሮ ለገንዘብም ማግኛ ምንጭ ሰጥቶ ይገኛል ።



ካቴድራሉ የሚያመራቸው የሥጋጃ ዓይነቶች ።



ሐ/ የሙካሽ ሥራንም አስፋፍቶ በመሥራት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሊያለብስ ችሏል ። አልባሳትን አዘጋጅቶ ማቅረብ የቤተ ክርስቲያን ተግባር ሲሆን ፤ ይኸ ባለ



የሙካሽ ሥራ ።

መፈጸሙ ያልሆኑ ሰዎች በመስላቸው እያሰፉና እያሠሩ በማቅረባቸው ቤተ ክርስቲያንን በሥነ ሥርዓት ጎድተዋት ይገኛሉ ።

መ/ ሱቆችን በየቦታው ከፍቶ የካቴድራሉን የገቢ መጠን በማዳበር ይሠራል ። ካቴድራሉ ወደፊትም በብዛት ወደዚህ የልማት ሥራ ለመሠማራት ዕቅድ አለው ። ምክንያቱም የገቢ ምንጭ ከሌለ ይኸ ሁሉ ሥራ ሊቋረጥ ይችላልና ። የገቢ ምንጭ ለመሥሪያ ቤት ፤ የደም ሥር ደግሞ ለሰው አካል በግድ ያስፈልገዋልና ።



ታቦታቱ የሚለብሱ የሙካሽ ሥራዎች ።


www.ethiopianorthodox.org

## ፰ኛ ፤ ጥንታዊ ቅርስ ፤—

ካቴድራሉ ጥንታውያን የሆኑ ብዙ የብራና መጻሕፍትና የመጀመሪያው የማኅተም መኪና እንደመጣ የታተሙ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ፤ እንዲሁም ልዩ ልዩ አስረጅነት ያላቸው ሰነዶችን የያዘ ጥንታዊ የቅርስ ክፍል አለው ። እንዲሁም በንዋየ ቅድሳት በኩል በሌላው ደብርና ገዳም የማይገኙ ንዋያተ ቅድሳት ፤ አልባሳት ፤ በብዛት ይገኛሉ ። ከዚህም ሌላ ዛሬ ዘመናችን ያፈራቸው መጻሕፍትን ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳትን ፤ አልባሳትን እየገዛና እያሠራም ያስቀምጣል ። በዚህ ክፍል በብዛትና በዓይነት ልዩ የሆኑ ዕቃዎች ስለሚገኙ የጎብኝዎችን ዓይን የሚማርኩ ፤ ስሜታቸውን የሚያረኩ ዕቃዎች እንደሚገኙ በማመን የውጪ አገር ጎብኝዎች በብዛት ይጎርፋሉ ። ለዚህም ክፍል ልዩ አስተዳደር አለው ። አሁንም ፤ የመጎብኛውን ዕለት ፤ ሰዓት ወስኖ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል ።

## ፱ኛ ፤ በጎ አድራት ፤—

የቤተ ክርስቲያን ሥራዋ ፤ ትምህርቷም ከበጎ አድራጎት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ፤ ካቴድራሉ ለልዩ ልዩ የበጎ አድራጎት ድርጅት በየዓመቱ የገንዘብ ልግሥና ያደርጋል ። በአካባቢውም የተወሰኑ ችግረኞችን ይዞ ይረዳል ። ወደፊትም ከዚህ በበለጠ ለመሥራት ዕቅድ ሲኖረው ፤ ከላይ የተዘረዘረው ሁሉ የበጎ አድራጎት ሥራ በመሆኑ ብዙውን እንደፈጸመ የሚያስቈጥረው ነው ።



[illegible]

የመንበረ ፀባዖት ቅ. ሥ. ካቴድራል የ፲ ዓመት የሥራ ውጤት ።

## ፲ኛ ፤ የሕዝብ ግንኙነት ፤—

ከጥንት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን የድኃው ፤ የባለጸጋው መሰብሰቢያ ፤ የአጣው መለመኛ ፤ ያገኘው ማመስገኛ ፤ የተጨነቀው መማጠኛ ፤ በጠቅላላም የእገሌ ቤት ፤ የእገሌ ድርጅት ሳትባል ሁሉም የሚገናኙባት ቦታ ናት ። አሁንም ሕዝብን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚስብና ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚያስተዋውቅ ድርጅት ካቴድራሉ አቋቁሞ በመሥራት ላይ ይገኛል ። ይኸውም

፩ኛ/ በአጥቢያው የሚገኙትን ምእመናን በሰፈር ሹምና በዕድር ዳኞች አማካይነት የማኅበራዊ አገልግሎት ፤ የጸሎትም ሥነ ሥርዓት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይጐተጉታል ።

፪ኛ/ ከሌላም አጥቢያ ቢሆን ችግር አግኝቷቸው የመጡትን ፤ መንገድ የጠፋቸውን የሚመራና ምክር የሚሰጥ የማኅበራዊ ግንኙነት የሚፈጥር ድርጅት አቋቁሞ በመሥራት ላይ ይገኛል ።

በጠቅላላም የእያንዳንዱን የ፲ ዓመት የሥራ ውጤት እንመልከት ።



www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት

## የ፲ ዓመት የሥራ መግለጫ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአፍሪቃ አህጉር የመጀመሪያዋ የክርስትና ሃይማኖት አንጋፋ ናት ። « የክርስቲያን ደሴት » የሚል ሥያሜ ለማግኘት የበቃችበትም ምክንያት ከመጀመሪያው መቶ ዓመት ጀምሮ የክርስቶስን ወንጌል በመቀበል ፤ ደረጃ በደረጃ እያደገችና እየተስፋፋች በመራመድ ላይ ሳለች ፣ በሺኛው መቶ ዓመት ደግሞ የተሻለ መልካም ዕድል አጋጥሚታል ።


ይኸውም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ አርቆ አሳቢነትና የአመራር ብልህነት የክርስትና እምነት ፤ የሳይንስ ጥበብ ባስገኘው መሣሪያ ማሠራጨት ተፈላጊ መሆኑን አምነውበት ከዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ድርጅት « LWF » ጋር ልዩ ስምምነት አድርገው የብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ አዲስ አበባ ከተማ ተቋቁሞ ለአፍሪቃና ለእስያ አህጉረ ዓለማት የወንጌል ስብከት እንዲያስተላልፍ ፈቀዱ ።

### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት አቋምና የሥራው አመራር ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለክርስቶስ ያላት እምነትና ትምህርት ጥንታዊ መሆኑ በታሪክ ተመስክሯል ። ይሁን እንጂ የወንጌል ስብከት ( ትምህርት ) በተስተካከለ ሁኔታ ለመላው ሕዝብ እንዲዳረስ ዘመናዊ የሥራ እንቅስቃሴ ለማሳየት ይህ ዓይነት ድርጅት እንዲቋቋም አስፈለገ ። ስለዚህም « የሃይማኖት ጋሻ » የሆኑ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ቻርተርድ በሆነው በመንበረ ፀባዖት ቅ/ ሥላሴ ካቴድራል ሥር ይህ ድርጅት እንዲቋቋም አድርገዋል ።

### ዓ ላ ማ ው ፤

የዚህ ድርጅት ዋና ዓላማ ፣ በአራት ታላላቅ ክፍሎች የተከፈለ ነው ። ይኸም ፤



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ጽ/ቤት ።

፩ ክክርስትና ውጭ የሆኑትን ሕዝቦች ወደክርስትና መመለስ ፣

፪ ክርስቲያኖችን ሕዝብ ማጽናትና በወንጌል ትምህርት ማበረታታት ፣

፫ ለከተማው ሕዝብ ፣ የከተማ ሐዋርያዊ ተግባርን ማስፋፋት ፣

፬/ ከኢትዮጵያ አልፎ ወደሌሎች የአፍሪካ አህጉር የሚላኩ ወንጌላውያንን ማሠልጠን ፣ ድርጅቱ በሥሩ የሚያስተዳድራቸው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ባለፉት ፲፤ ዓመት የተፈጸሙትን

www.ethiopianorthodox.org

ዋና ዋና ሥራዎች በአስተዋጽኦ መልክ ይዘረዝራል ።

## የሬዲዮ ስቱዲዮ ክፍል ፤

ሀ) በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ አማካይነት ዘወትር ማታ ማታ በሚሰጠው የግማሽ ሰዓት ፕሮግራሙ በአጭር ሞገድ (ሾርት ዌቭ) ለጠ/ግዛቶች ፤ በመካከለኛ ሞገድ (ሚዲየም ዌቭ) ለአዲስ አበባና ለአካባቢው ሕዝብ በ፲ ዓመት በ፩ሺ ፰፻፴ ሰዓቶች ፤ በ፲ሺ፰፻፶ አርእስቶች፤ መንፈሳዊ ትምህርት ፴ በመቶ፤ ማኅበራዊ ኑሮ፤ ፴ በመቶ ፤ ልማት ፳፰ በመቶ ፤ መዝሙሮችንና ሌሎች ትምህርቶችን ፲፪ በመቶ በልዩ ልዩ ዘመናዊ የአቀራረብ መልክ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አበርክቷል ። ስለሰጠውም መንፈሳዊ ትምህርት አጥጋቢነትና ተወዳጅነት ከአድማጮች በሚደርሱን የአስተያየትና የምስጋና ደብዳቤዎች ለመረዳት ችለናል ።



ስብከትን በስቱዲዮ ።

## የድርጅቱ ድርሰት ክፍል

በየወሩ እየታተመ የሚወጣው «ድምፀ ተዋሕዶ» ጋዜጣ በአቀራረቡም ሆነ በሥነ ጽሑፍ ደረጃ ስለተሻሻለ ፤ በሕዝብ ዘንድ በጣም ተወዳጅ በመሆኑ የሚገዙ ተኞች ቁጥር እየተጠለ ሔዷል ። የሚታተመው ጋዜጣ በሙሉ ለምእመናን ስለሚደርስ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ይዞታ አለው ፤ እስከ አሁንም በ፩ሺ፱፻፰ አርእስቶች በዓይ





ለማርያም ድርጅት የሚታተሙ ልዩ ልዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች ።

በማዘጋጀት እስከ ፪፲፪ ቍጥር ድረስ ታትሟል ። በየጊዜውም «ትንሣኤ» የተባለው የቤተ ክርስቲያንን ባህልና ሥነ ሥርዓት ፤ ሃይማኖታዊ ትምህርትን ፤ ለሕዝብ የሚያበረክት መጽሔት እስከ ቍጥር ፺ ድረስ አትሟል ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሰፊው የሚያብራራ በእንግሊ



www.ethiopianorthodox.org

ዝኛ ቋንቋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን Ethiopian Orthodox Church በሚል ርእስ አሳትሞ የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ሥርዓት ለሕዝብ አበርክቷል ። በሬዲዮ የሚተላለፈውን ትምህርት ሁሉ የሚያዘጋጅ ይኸው ክፍል ነው ።

## የተዘዋዋሪ ጓድ የስብከት ክ ፍ ል ፤

የድርጅቱ ሰባክያን በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ በዓለም በቃኝ ፤ በጠባይ ማረሚያ ፤ በመንፈሳዊ ማኅበሮች እየተሠማሩ ያስተምራሉ ። የድርጅቱ የሥነ ምግባር ጓድ (የተዘዋዋሪ የሞራል ጓድ) በአዲስ አበባ በሚገኙ የመንግሥትና የግል ት/ ቤቶች ፤ ዕድሮች ፤ በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ፤ በታላላቅ በዓላት እጅግ ብዙ ለሆኑ ምእመናን በስብከት በግጥምና በድራማ መልክ መንፈሳዊ ትምህርትን ሰጥቷል ። ከማኅበሮቹ ሹማምንት ጋር ተስማሚ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም በማውጣት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በየሳምንቱ እሑድ ለወጣቶች የሚሰጠውን ፕሮግራም በተሻለ መልክ በሚገባ ያከናውናል ።

## የትምህርት ክፍል ፤

ሀ) የድርጅቱ ሰባክያን በዕረፍት ጊዜያቸው ያስተምሩበት የነበረው የሥላሴ ትምህርት ቤት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ በመሔድ ከ፩ኛ እስከ ፲፩ኛ ክፍል ድረስ በመክፈት ወንዶችንና ልጃገረዶችን በማስተማር ፤ ምርጥ መምህራንን በመቅጠር በአሁኑ ጊዜ ፲፰ ኢትዮጵያውያን መምህራን በበጎ ፈቃደኝነት ፤ በመምህርነት ከሚያገለግሉ ፩ የውጭ አገር ሰዎች ጋር የመምህራን ዓይነት ቁጥርም ፤ ስለበዛ በዚህ ት ቤት የሚማሩት ተማሪዎች ብዛት በየጊዜው እየጨመረ ሔዷል ። በተጨማሪም በየዓመቱ ብዛታቸው ከ፹ በላይ የሚደርስ ተማሪዎችን በነፃ ያስተምራል ።

በየዓመቱ የ፷ኛንና የ፰ኛን መልቀቂያ ፈተና የሚወስዱት ተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ መሔዱ ብቻ ሳይሆን፤ለፈተና የሚያስቀምጣቸው ሁሉ ለማለፍ በመቻላቸው ት/ ቤቱ ስመ ጥሩ ሆኗል ። የሚሰጠውም ትምህርት ከመንፈሳዊ ትምህርት ጋር የተጣመረ በመሆኑ ጥሩ ኢትዮጵያውያን ዜጋዎችን ለማዘጋጀት የሚበቃ ነው ።

ለ) ወልመራ እማሆይ ደብሪቱ ጠብቃቸው በለገሡት ፳ሺ ሜትር ካሬ ቦታ ላይ የተቋቋመው የአባ ወልደ ማርያምና የእማሆይ ደብሪቱ ት/ ቤት ከ፩—፯ ክፍል ሲኖረው ብዙ ልጃገረዶችና ወንዶች ተማሪዎች ይማራሉ ። በየዓመቱም ፳፭ ተማሪዎችን ያለ መመዝገቢያ ያስተምራል ፤ ፯ መምህራን በዚህ ት/ ቤት ውስጥ ያገለግላሉ ።

ሐ) በጐጃም ጠ ግዛት በመተከል አውራጃ በቡለን ቀበሌ የተቋቋመው ት/ቤት በአካባቢው የሚገኙትን የነገደ ሻንቅላ ፤ ጋላ ፤ ሽናሻና አማራ ልጆችን በነፃ ያስተምራል ። ከ፩—፯ ክፍል ሲኖረው ፯ መምህራንና ፩ ዘበኛ ያገለግላሉ ። በትምህርት ቤቱም አካባቢ በየዓመቱ የእርሻ ሙከራ ስለሚደረግ ጥሩ ውጤትን በማሳየት ላይ ነው ። በአካባቢው የሚኖረው ሕዝብ የልብስንና የመድኃኒትን ጥቅም ባለማወቁ ራቁቱን እየሔደ በሕመም ይቸገር የነበረውን ፤ ድርጅቱ ከቀይ መስቀል ማኅበር ርዳታ ጠይቆ የልብስን ጥቅም አስተምሮ በየጊዜው ለመልበስ አብቅቷቸዋል ።

በአሜሪካ ፕሬስቢቴሪያን ሚሽን የፕሮግራም ጥና ጸሐፊ ሚስተር ክርስቶስና ዶክተር ቫንዴል (የኦርቶዶክስ ግንኙነት ኃላፊ) ርዳታ በግል አኢሮፕላናቸው ሔደን ትምህርት ቤቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ጐብኝተናል ። በአካባቢው ከሚገኘው ሕዝብ ጋር ተገናኝተን ስለትምህርት ቤቱ ዕድገት በሰፊው ተወያይተን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ለዚሁ ት/ ቤት ማስፈፊያ የተሰጠውን ርዳታ እንደተቀበለ ትምህርት ቤቱን የሚያሠራ መሆኑንና በአካባቢውም የሚገኘው ሕዝብ ፩ሺ (አንድ ሺ ብር) ርዳታ እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል ።

ለዚሁ ት/ ቤት ማሠሪያ ከዚህ በፊት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት በተጠየቀው ርዳታ መሠረት ፬ሺ፯፻፵፬ ብር ከ፶ ሳንቲም (አራት ሽህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) የተረከብን ሲሆን ቀሪውን በመጠባበቅ ላይ ነን ።

መ) በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የምትተዳደረው ከአዋሽ ወንዝ አጠገብ በተለይ ስሙ መልካ ቁንጥሮ በሚባለው ቦታ በወላሞ ሶዶ መንገድ ከአዲስ አበባ ፶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ባለችው ደብረ ፀሐይ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ ያሠራው « ደብረ ፀሐይ ኪዳነ ምሕረት ት/ ቤት» በ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. ጀምሮ በድርጅቱ ሥር እንዲተዳደር ተደርጎ ስለነበር አስተማሪዎችና ክፍሎችም ስለተጨመሩ ት/ቤቱ ከ፩—፫ ክፍል ከፍቶ ወጣቶችን እነ ስተኛ ገንዘብ በማስከፈል ያስተምራል ። በዚሁ ት/ ቤት ፫ መምህራን ያገለግላሉ ።

## የእሑድ ት. ቤቶች ።

ከተዘዋዋሪ የሥነ ምግባር ጓድ ሌላ በየሳምንቱ እሑድና ቅዳሜ በጠባይ ማረሚያና በወህኒ ቤት እንዲሁም ወጣቶች በሚገኙባቸው ቦታዎች የድርጅቱ መምህራን እየሔዱ ያስተምራሉ ።



## ማኅበሮች ፤

በድርጅቱ ሥር የሚተዳደሩ የወጣቶች ሴቶች ማኅበር «ማኅበረ ክርስቶስ» የወንዶች ማኅበር «ማኅበረ ሥላሴ» የተባሉትን ማኅበሮች ድርጅቱ በሥሩ ያካሔዳል ። ለእነዚህም ማኅበሮች የሥራ ማስኬጃ በየወሩ $ 100.00 እየሰጠ በየጊዜው ለሚያደርጉት የመንፈሳዊ ትምህርት እንቅስቃሴ ሁሉ እየተቈጣጠረ ያበረታታቸዋል ። እነዚሁም ማኅበሮች በየበኩላቸው የእሑድ ትምህርትንና ልዩ ልዩ ሙያዎችን ለወጣቶች በማበርከት ላይ ይገኛሉ ።

## የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ክ ፍ ል ።

ድርጅቱ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት አንድነት ማኅበር ቋሚ አባል ስለሆነ በማኅበሩ የሚዘጋጁትን ልዩ ልዩ ሴሚናሮች በመካፈሉ ብዙ ጠቃሚ ሥራዎችን ለማከናወን ረድቶታል ። ብዙ ማኅበራዊ ኑሮን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ከመሰል ድርጅቶች ጋር ተሰልፎ አከናውኗል ።

## የዕድገት ኮሚቴ ።

ከ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ጀምሮ በድርጅቱ ሠራተኞች ከወር ደመወዛቸው ላይ ፩ በመቶ ያዋጡት የነበረው ገንዘብ ጥሩ ውጤት እንዲያገኝ ፱ አባሎች ያሉበት «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት የዕድገት ኮሚቴ» የድርጅቱ የበላይ አስተዳዳሪ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ እንዲቋቋም ፈቅደዋል ። የዕድገቱ ኮሚቴ የድርጅቱ የገቢ ምንጭ የሚገኝበትን ዘዴ እያጠና ያቀርባል ።

ይኸው ኮሚቴ በርካት ያሉ ስብሰባዎችን ካደረገ በኋላ ለዚሁ የሥራ አፈጻጸም ቋሚ ደንብ አውጥቶ ለድርጅቱ የበላይ

www.ethiopianorthodox.org

አስተዳዳሪ ቀርቦ ጸድቋል ። እስካሁን የተሰበሰበውን የ፩ በመቶ መዋጮ ገንዘብ አዲስ መኪና እንድትገዛበት አድርጓል ።

## ግ ን ኙ ነ ት ።

ድርጅቱ ከሀገርም ሆነ ከልዩ ልዩ የውጭ ሀገር ድርጅቶች ጋር በአለው ጠንካራ ግንኙነት መሠረት በ፲ ዓመታት ከፈጸማቸው ጉዳዮች በመጠኑ ፤ ፩/ ወደ ሮማንያና ወደ ግሪክ ወጣቶችን ከመላኩም ሌላ በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ትምህርታቸውን ፈጽመው ከተመለሱት ከአባ መዓዛ ቅዱሳን ገ/ሕይወትና ከአቶ አእምሮ ማንደፍሮ ሌላ የድርጅቱ ቀዋሚ ሰባኪ መላከታቦር ተሾመ ዘሪሁንን ለከፍተኛ የሃይማኖት ትምህርት በሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር አማካይነት ወደ እንግሊዝ አገር ልኮ ቤተ ሰባቸውን በመጠነኛ ገንዘብ እየረዳ እንዲማሩ አድርጓል ።

፪/ ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ የተባሉትን ( ቀዋሚ ሰባኪ ) ወደ ሩማንያ ለከፍተኛ የሃይማኖት ትምህርት ልኮ እንደዚሁ ቤተሰባቸውን በመጠነኛ ገንዘብ ይረዳል ።

"World Brothers Foundation"

፫/ ሚ/ ር ኬንት ጊልበርት ግሮሽና ባለቤታቸው ሚስ. አን ሮዝሊን ግሮሽ በድርጅታችን በበን ፈቃድ ለማገልገል ስለመጡ በሥላሴ ት/ ቤት በአስተማሪነት በመሥራት ላይ ይገኛሉ ። ከዚህም ድርጅት ሚስ.ጋሬት ሮነቶድ በድርጅታችን አማካይነት መጥተው ያገለግላሉ ። ከሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበርም ሚስተር ዳዊት ስቶክስ ቀደም ብለው በሥላሴ ት/ ቤት ያስተምሩ ስለነበር ፤ በርሳቸው ምትክ ሚስተር ኮሊን ማንስል ያስተምራሉ ። በእሑድ ት/ ቤትም ሚስ. ዶረስ ቤገስንና ሚስ ቬራ ጀርቢስ አገልግሎታቸውን በማበርከት ላይ ይገኛሉ ።

እንዲሁም ከአሜሪካን ፕሬስቢተሪያን ሚሲዮን ሚስተር ፍሬድ ዊልሰን ፤ ሚስተር ቫንኢግን ከነባለቤታቸው ለተመሳሳይ አገልግሎት ተሰልፈዋል ።

፬/ LWF ጋር በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ አማካይነት ባለን ግንኙነት ለሬዲዮ ፕሮግራማችን ማሻሻያና ለልማት ፕሮግራሞች አገልግሎት የሚውል ፤ ፲፭ሺ ( አሥራ አምስት ሺ ብር ) በዚህ ዓመት ለማግኘት እንደምንችል ቃል በሰጡን መሠረት ፲ሺ፯፻፺ ብር ከ፺፯ (አሥር ሺ ሰባት መቶ ስድስት ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም) ተረክበን በሥራ ላይ ውሏል ።

፭/ አቶ አእምሮ ወንድማገኘሁ በግ. ን. ነ. ልዩ ካቢኔ የመንፈሳዊ ክፍል ዳይሬክተርና አቶ አበባው ይግዛው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የነበሩት «እስላም በአፍሪካ » በተባለው ጉባኤ ላይ ለመገኘት ወደ ኬንያ ሔደው ከሚያዝያ ፳፭ —፳፯/፷፬ ዓ. ም. በድርጅቱ ስም ተካፍለዋል ።

ከዚህም በፊት መልእክተኞቹን በመላክ በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ላይ ተካፋይ በመሆኑ በብዙ አህጉር የታወቀ ሆኗል ።


፮/ የሱዳን እንተርየር ሚሲዮን በመተከል ለሚገኙ ሠራተኞቻችን ቀለብ ስለሚያስተላልፍልን በተለይም ቦታውን ስንገመግም የአየር ማረፊያው በሚገባ እንዲሠራ ስለረዱንና ስለሚረዱንም ውለታ አለብን ።

ይህ ሁሉ እንዲፈጸም ለድርጅቱ የጣሩት የበላይ አስተዳዳሪው ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ስለሆኑ ድርጅቱ ምን ጊዜም ይኮራባቸዋል ።

ሐዋርያዊ ድርጅት

# የሥላሴ ትምህርት ቤት እንዴት ተጀመረ ?

የሥላሴ ትምህርት ቤት መስከረም ፲፬ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ. ም. በማታ ትምህርት ተጀመረ ። ዋና ዓላማውም የጥንቷ የቅድስት ሥላሴ ት/ቤት ፩ኛ ደረጃ ስለተዘጋ የካቴድራሉን አገልጋዮች በዘመናዊ ትምህርት ለማሠልጠን በማሰብ ነው ፤ ት/ቤቱን የከፈቱትም ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ናቸው ። ለጊዜው የነበሩ አስተማሪዎች አቶ ታደሰ ኃይለ ሥላሴ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ፤ አቶ ብርሃኔ ለወግነህ ለተወሰነ ክፍለ ጊዜ ሲቀጠሩ ሌሎችም በበጎ ፈቃድ የሚረዱ ነበሩ ፤ ለጊዜው ተማሪዎቹ ስምንት ብቻ ነበሩ ። በዓመቱ በ፶፯ ዓ. ም. ግን ትምህርት ቤቱ መልኩን ለውጦ በቀንም እንዲማሩ ስለተደረገ ክፍሉ ከ፩ኛ እስከ ፬ኛ ደረሰና አቶ ኢያሱ ፤ አቶ ከሃሊ ዓለሙ የተባሉ እንዲያስተምሩ በተጨማሪ ተቀጠሩ ። ተማሪዎቹም ፴፱ ያህል ደረሱ ። ይህ ት/ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ለሚገኙት መነኮሳትና ዲያቆናት የዘመናዊውን ትምህርት መስጠት የጀመረበት ጊዜ ስለሆነ በጊዜው በትምህርት ከተሰለፉ ዲያቆናትና መነኮሳት ለአብዛኞዎቹ ዘመናዊው ትምህርት የማይጨበጥ ፤ የማይረገጥ መስሎ ስለታያቸው ለተወሰኑ ዓመታት በጣም ችግር ፈጥሮ ነበር ። በተጨማሪም ልናስበብት የሚገባን ነገር ቢኖር ምንም ተማሪዎቹ ከቤተ ክርስቲያን አካባቢ ቢመጡም በዕድሜ አለመመጣጠን ስለነበር ትምህርት ፤ ቶሎ የመቅሰም ችሎታ ያላቸውንና የሌላቸውን ተማሪዎች ለይቶ ማወቅ ሌላ ችግር ነበር ።



ለመጀመሪያ ጊዜ የዲያቆናትና [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ማሠልጠኛ ክፍል ፤

በዚሁ ዓመት የሬዲዮ ስብከት በካቴድራሉ ኃላፊነት ስለተጀመረና ሐዋርያዊ ድርጅት ስለተቋቋመ ፤ ፩ ክፍል የሰባክያን ማሠልጠኛ ተከፈተ ፤ ስለዚህ በጠቅላላው የትምህርት ቤቱ ክፍል ወደ ፳ ክፍል ደረሰ ። በዚህን ጊዜ የሐዋርያዊ ድርጅት ሠራተኞች በመላ ቀዋሚ አስተማሪዎች ሁነው የነፃ ትምህርት ለመስጠት ተመደቡ ። እነሱም አቶ መስፍን እምባቸው ፤ አቶ ዘመድሁን ብዙወርቅ ፤ አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ ፡ አቶ አእምሮ ማንደፍሮ ፤ አቶ ግርማ ወ/ ቂርቆስ ፤ አቶ አበራ ተፈሪ ፡ ቄስ ሰሎሞን ገ/ሥላሴ ናቸው ። ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ቄስ ልሳኑ በዛብህ ፤ አቶ ከሃሊ ዓለሙ አባ መዓዛ ቅዱሳን ያስተምሩ ነበር ። ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያምም ከዚያ ሁሉ ፤ ከባድ ሥራቸው ጋር ተጨማሪ ሥራ አድርገው አስተምረዋል ። መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈም የኮርሱ መሪና አስተማሪ ነበሩ ።

በዚህም ጊዜ ጥብቅ እርምጃና ቁጥጥር እየተደረገ ቤተ ክርስቲያኑን በዲቁናም ሆነ በቅስና የሚያገለግል ማንኛውም መነኮሴና ዲያቆን በሙሉ እዚሁ ት/ቤት ውስጥ ገብቶ ዘመናዊውን ትምህርት መሳተፍ ግዴታ እንዳለበትና መጀመሪያም ለመነኮሳትና ለዲያቆናት ተብሎ እንደ ተደከመበት ጥብቅ ትእዛዝ ለሁሉ ተላለፈ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች በትእዛዙ መሠረት ት/ ቤት መግባት ግዴታቸው መሆኑን ተገንዝበው፤ሁሉም ለትምህርት ተሰለፉ፤መ/ ቤቱም በበኩሉ ሌላ ተጨማሪ ክፍል ማዘጋጀት ግዴታው መሆኑን ስለ ተረዳው ፤ መጀመሪያ ከምትገኘው ክፍል ጋር ተያይዘው ለሌላ ሥራ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩትን ክፍሎች ከሌላ ሥራ ይልቅ ለትምህርት ቤት እንዲያገለግሉ በማድረግ በሰፊው እንዲማሩ አደረገ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪዎቹ በችሎታ መለያየት፤በደረጃ የሚለያዩ ክፍሎችንና ተጨማሪ መምህራንን ማስፈለጉ ግድ ሆነብን ። ስለዚህ መ/ ቤቱ የተነሳበትን ዓላማ እስከ መጨረሻው ግብ ለማድረስ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማለትም ቅኔን ፤ ዜማን የመጻሕፍት ትርጓሜንና የመሳሰሉትን ዕውቀት ይዘው እንደገና ዘመናዊውን ትምህርት እንዲያጠኑ ያስለፋቸውን ተማሪዎች ለማስተማር የሚችሉ የበቃ ችሎታ፤የነቃ አእምሮ ያላቸውን መምህራን ቀጥሮ በሰፊው ማስተማር ከፍተኛ ዓላማው አደረገ ።

የውጪ ተማሪዎችን መቀበል እንዴት
እንደተጀመረና

# የትምህርት ቤቱ ግሥጋሴ

ካቴድራሉ ትምህርት ቤት ሠርቶ ፤ መምህራን ቀጥሮ ማስተማር ከጀመረ ወዲያ የትምህርት ጥማቸውን ለማርካት የሚጓጉ ያካባቢው ወጣቶችና በገንዘብም ሆነ ወይንም ባንዳንድ ችግር የትምህርትን ጣዕም እያወቁ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ዓለም ለመላክ የማይችሉ ወላጆችን ችግር በመገንዘብ፡መፍትሔ የሚገኝበትን ዘዴ እየፈለገ ትምህርት ቤቱ ይረዳ ጀመር። ግን እዚህ ላይ አተኩረን ማየት ያለብን የተማሪ ብዛት ፤ የመምህራን እጥረት ጉን ለጉን አለመሄዳቸው ነው።ስለዚህ ትልቁ ችግር ሌሎች ተጨማሪ መምህራን መቅጠር ነበር ፤ ሆኖም የቤተ ክርስቲያን እንዱ ዓላማ ይህንን የመሳሰለውን ችግር ለማቃለል ስለሆነ በአካባቢው የሚገኙትን ጫማ ጠራጊዎች ፤ መጽሔት፤ ጋዜጣ ሻጮችን በነጻ ተቀብሎ ማስተማር ጀመረ ትምህርት ቤቱ እያደገ ፤ ተማሪው እየበዛ ሲሔድ ት/ ቤቱን ከት/ ሚኒስቴር ጋር ማስተዋወቅ በግድ አስፈለገ ። የትምህርት ሚኒስቴር ተቆጣጣሪዎችም/ ሱፐርቫይዘሮች / ከዚህን ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው እየመጡ የት/ቤቱን አቋም መመልከት ጀመሩ ። ምንም እንኳን ት/ ቤቱ ገና ሲቆረቆር በት/ ሚኒስቴር ሥርዓተ ትምህርት ቢረዳም የራሱን የውስጥ ደንብ በየጊዜው እያሻሻለ አሁን ካለበት ደረጃ ለመድረስ ችሏል ። የተማሪዎቹ በቋንቋም ሆነ በሌላ የቀለም ትምህርት ሠልጥኖ መገኘት የት/ ቤቱ ዋና ዓላማ ስለነበር ከሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር በእንግሊዝኛ ቋንቋና በሌላ ትምህርት ሊረዱን የሚችሉ አንድ እንግሊዛዊ ጠይቆ ለማግኘት ቻለ ፤ ለጊዜው ለዚህ ተግባር ፈቃደኛ ሁነው የቀረቡ ሚስተር ዳዊት እስቶክስ የተባሉ ወንጌላዊ ነበሩ ።

በዚያን ዘመን ት/ቤቱ የእጅ ሥራ ፤ የሥዕል ትምህርት አይሰጥም ነበር።ነገር ግን የሃይማኖት ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክና የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ትምህርቶች ከሌሎች ዘመናዊ ትምህርቶች ጋር በማጣመር ይሰጥ እንደነበር ግልጽ ነው ።ሆኖም ዓመት አልፎ ፡ ዓመት ሲተካ ት/ ቤቱ በነጻ ማስተማሩን የሰሙና የተመለከቱ ያካባቢው ችግረኞች ወላጆች ፤ ልጆቻቸውን ት/ ቤት ተቀብሎ እንዲያስተምር ችግራቸውን በደብዳቤ እየገለጹ አቤቱታና ልመና ጀመሩ ።

ነገር ግን ት/ቤቱ ማንኛውንም ችግረኛ ነኝ የሚለውን መቀበል ግዴታው ስላልነበር ፡ በየመቱ ልዩ ኮሚቴ እየተቋቋመ ችግረኞቹን እየመረጠ፤በትምህርታቸው ጉበዝ ፤ ባነጋገራቸው ጥራት ያላቸውን የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ በመቀበል እስከ ፲፱፻፷ ዓ.ም. ቆየ፤ምንም እንኳን የውጭ ተማሪዎች በችግራቸውና በትምህርታቸው እየተመረጡ ቢገቡም በየመቱ መጀመሪያ ላይም ሆነ በየመቱ አጋማሽ ፤ ልጁን ት/ቤት ለማስገባት የሚጐርፈው ሕዝብ እየበረከተ ስለሔደ ፤ ት/ቤቱ መጀመሪያ ከተቆረቆረበት ቦታ አልፎ ፡ ተርፎ ባሁኑ ጊዜ ት/ቤቱ ወደሚገኝበት ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ተዛወረ ። አዳራሹን በሚገባጠም ማነቃ ለሦስት ክፍሎ ተጨማሪ ክፍል በማድረግ በመጀመሪያ ጊዜ በ፲፱፻፷ ዓ.ም.በዛ ያሉትን የውጭ ተማሪዎች ተቀብሎ ማስተማር ጀመረ ።

እንዲያውም በዚህን ጊዜ ተማሪዎቹ እስከ ፫፻ - (ሦስት መቶ) ይደርሱ ነበር ። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ እስካለንበት ዓመተ ምሕረት ድረስ ፤ የተማሪዎቹን፤ የመምህራኑንና የክፍሎቹን ብዛት በሰንጠረዥ መምሪያ መሠረት ሊረዱ ይችላሉ ።

በዚሁ ዓ.ም. «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት» በሚል ስም የሚጠራው ት/ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ፰ኛ ክፍል ለብሔራዊ ፈተና አስቀምጦ ልጆቹን በሚያስደንቅ ሁኔታ ሊያሳልፍ ቻለ ። የት/ቤቱ ቁንጮ የሆኑ ሦስት ዲያቆናት በመጀመሪያ ጊዜ ያስተማርናቸው ፈተናቸውን በጥሩ ሁኔታ አልፈው አሁን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ በመንፈሳዊ ኮሌጅ የ፫ኛ ዓመት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ የመጀመሪያውን ትምህርት ሊወስዱ የቻሉ ከዚሁ ት/ቤት ነው ። እነርሱም ዲያቆን ብርሃነ መስቀል ፤ ዲያቆን ተስፋዬ መርሐ ፤ ደብተራ መላኩ አዘነ ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org



የአንደኛ ደረጃ የሥላሴ ት/ቤት ።

በተለይም በ፲፱፻፷ ዓ. ም. ያካባቢው ወላጆች ልጆቻቸው እዚሁ መንፈሳዊ ት/ቤት ገብተው እንዲማሩላቸው ዋና ምኞታቸው ስለነበር ፤ ልጆቻቸውን እየያዙ የሚመጡትን ወላጆች የመጡትን ልጆች እየተቀበለ ማስተማር ሲጀምር ፤ በዚሁ ት/ቤት ለሚገኙ ተማሪዎች ብዛት በር ካታ መምህራን ስላስፈለጉን፡ከውጭ ካገኘናቸው ከበጎ ፈቃደኞች ሌላ ፤ የኢትዮጵያውያንን መምህራን ብዛት ወደ ስድስት አደረሰው ። (ሰንጠረገዥ ላይ ይመልከቱ) እንደገና በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. አዲስ የትምህርት ምዕራፍ ተከፈተ ። ይኸውም በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ስድስተኛን ክፍል ብሔራዊ ፈተና ያለፉ ተማሪዎች በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. ፰ኛ ክፍል ገብተው በሚያስደንቅ ሁኔታ የ፰ኛን ክፍል ብሔራዊ ፈተና ስላለፉ ነው ።

በ፲፱፻፷፬ ዓ.ም.ስምንተኛን ክፍል ያጠናቀቁትን መነኮሳትና ዲያቆናት በተለየ መንገድ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለማሠልጠን ታስቦ፡አንድ ልዩ ፕሮግራም ተዘጋጅና ሙሉ የመንፈሳዊ ትምህርት የዓመት ኮርስ ተሰጠ ፤ በዓመቱም መጨረሻ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚሁ ሙያ የሰለጠኑና ትምህርቱንም በሚገባ ያጠናቀቁ መነኮሳትና ዲያቆናት ከሊቀ ሥልጣናት እጅ የምስክር ወረቀት ተቀበሉ ።

በዚሁ ዕለት ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም የመጡትን ተማሪዎች ለመቀበል እንዲያመች ሲናገሩ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. አዲስ ት/ቤት በከፍተኛ ዋጋ እንደሚሠራና ት/ቤቱንም ያካባቢው ወላጆች እንደሚመሩት በበዓሉ ላይ ለተገኘው ሕዝብ አበሠሩ ፤ ምክንያቱም እስካሁን ድረስ የነበረው ትምህርት ለሁሉም በነፃ ይሰጥ ስለነበር ፤ ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን በ፲፱፻፷፬ ዓ.ም. ባመቱ መጀመሪያና ባመቱ አጋማሽ ላይ ማንኛውም ተማሪ አምስት አምስት ብር እንዲከፍል ተወሰነ ፤ በዚህን ጊዜ ባመት እንኳን አሥር ብር ፤ በሳንቲም የሚቆጠር ገንዘብ ለመክፈል አለመቻላቸውን የገለጹ ወላጆች ስለበዙ ጥብቅ ጥናት ተደርጎ ስባ አምስት ተማሪዎች




ብቻ እንዲከፍሉ ሲደረግ፤ሌሎቹ በዓመት የተመደበውን ሂሣብ እየከፈሉ እንዲማሩ ተደረገ ፤ ይህም ሲባል መነኮሳትንና ዲያቆናትን አያጠቃልልም ።

## የፈተና ውጤት

የሥላሴ ት/ቤት በየጊዜው ለፈተና የሚያስቀምጣቸው ቍጥራቸው አነስተኛ የሆነ የ፯ኛና የ፰ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈታኞች ውጤት ያማረ በመሆኑና በአካባቢው የሚገኙ ወላጆች በትምህርት ቤቱ፤የትምህርት አሰጣጥና ሥነ ሥርዓት ይዞታ መደሰታቸውን መግለጽ ጀመሩ ። ሆነ በዘመናዊ ትምህርት ይሰለጥኑልን ነበር ። የሚል እሮሮም በአካባቢው ሲነገር መስማቱ ለጆሮ ይታክታል ።

## የአዲሱ የት/ ቤት ሥራ ።

የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወ. በፊት የነበሩት የመማሪያ ክፍሎች ጥበት ያላቸውና በዘመናዊ አቅድም ያል ተሠሩ መሆናቸውን በመገንዘብ ሠላሳ ሽህ ብር የፈጀ አሥር የመማሪያ ክፍሎች ሦስት መቶ ሕዝብ ሊይዝ የሚችል መሰብሰቢያ አዳራሽ በዘመናዊ አቅድ እንዲሠራ ወሰኑ ።




ለሁለተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የተሠራው ት/ቤት ።

ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የነበራትን የትምህርት አሰጣጥ ከፍተኛነትም በሰፊው የሚያስታውሱ በረከቱ ።

ቤተ ክርስቲያናችን በዘመናዊ የትምህርት አሰጣጥ በኩል ከፍተኛ ቦታን ብትይዝ ኖሮ ልጆቻችን በመንፈሳዊውም ይኸም ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በዘመናዊው ትምህርት አሰጣጥ በኩል ብትሰለፍ ጠንካራ መንፈስ ግብረ ገብነት ያላቸው ዜጎችን ለሀገርና ለወገን ለማትረፍ የምትችል መሆንዋን በመገንዘብ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org



በአንደኛ ደረጃ የሚማሩት የሥላሴ ት/ቤት ተማሪዎች ።



በሥላሴ ት.ቤት የሚማሩት ልጃገረዶች ።



የት/ቤቱ ሥራ ክንውን ተሚልቶ በ፲፱ ፻፷፫ ዓ. ም. በችሎታቸውና በትምህርት አሰጣጣቸው የሰለጠኑ መምህራን ተቀ ጥረው የሥራ አመራሩም ተሻሽሎ ሥራው በጥሩ ሁኔታ መካሔድ ጀመረ።

በት/ቤቱ የሚሰጡት የትምህርት ዓይ ነቶች የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ሥርዓተ ትምህርት የተከተለ ሆኖ በተ ጨማሪ ግእዝ ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ፤ ሃይማ ኖት ፤ መንፈሳዊ መዝሙሮች ፤ ሥርዓተ ጸሎትና ግብረ ገብ ናቸው ።

## በትምህርት ቤቱ የሚማሩ ተ ማ ሪ ዎ ች


፩- ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ዲያ ቆናትና መነኮሳት ።

፪- ከልዩ ልዩ የበጐ አድራጐት ድር ጅት የሚላኩ ፤

፫- በጣም ችግረኛ የሆኑ በጫማ ጠራጊ ነትና በጋዜጣ ሽያጭነት የሚተዳደሩ ።


፬- የት/ቤቱን ጥሩነት በመመልከት ከአካባቢው የሚላኩ ተማሪዎች ናቸው።

በተጠቀሰው ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ለ፯ኛ ክፍል ፈተና የቀረቡ ተማሪዎች በግራፍ እንደ ተመለከተው ፷፩ ሲሆኑ ከእነዚሁ ውስጥ ፷ ሲያልፉ አንድ ብቻ ወድቋል ። እንዲ ሁም ለ፰ኛ ክፍል ከቀረቡት ፲፰ ተፈታ ኞች መካከል ፲፬ ሲያልፉ አንዱ ብቻ ወድቋል ።





የ፮ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤትና ብዛት የሚያሳይ ግራፍ ።

www.ethiopianorthodox.org




የ፰ኛን ክፍል ተማሪዎች ብዛትና ውጤት የሚያሳይ ግራፍ ።




ከ፶፰—፷፭ ያለውን ውጤት የሚያሳይ መግለጫ ግራፍ ።



ይህ ውጤትና የወላጆችም ለት/ቤቱ ያላቸው ጉጉት ፤ የመምህራኑን ኃይልና የሥራ ፍላጐት እያበረታው ሔደ ። በዚህ ዓመት የነበሩት መምህራን ቊጥር ፲፫ ነበር ከነዚሁ ውስጥ አንዱ የውጪ አገር ዜጋ ሲሆኑ ፤ የቀሩት ችሎታቸው ከ፲፪ኛ ክፍል በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ነበሩ።

ከዚያም በ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. የተማሪዎቹ ቊጥር እየበረከተ በመሔዱ ፩፻፳፭ ደረሰ የመምህራኑም ቊጥር ፲፰ ነበር ። በዚህም ዓመት ለ፮ኛ ክፍል ፈተና ከተቀመጡት ፩፻፪ ተማሪዎች ውስጥ ፳፫ አልፈዋል ። ለ፰ኛ ክፍል ከተቀመጡት ፵፰ ተማሪ ዎችም መካከል ፵፫ በከፍተኛ ውጤት አልፈዋል ።

ይህም ሲባል ት/ቤቱ በየዓመቱ በሚ ሰጠው የብሔራዊ ፈተና ከዞኑ የት/ክፍል አንደኛና ሁለተኛ በመሆን ከፍተኛ ቦታ ማግኘቱ ተገልጿል ።


ከት/ቤቱ የ፰ኛ ክፍል ትምህርታቸ ውን ፈጽመው በሁለተኛ ደረጃ የተመ ደቡ ተማሪዎችም በውጤታቸው አላሳ ፈሩም ።

ነገር ግን «መጀመር ሲቀል መጨረስ ያውካል» የተባለው እንዳይፈጸም አርቆ አሳቢው ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማር ያም ወርቅ ነህ ፦

ሀ/ ከት/ቤቱ ፈጽመው በሁለተኛ ደረጃ በሌላ ት/ቤት የሚመደቡ ተማሪዎች የነበራቸውን የሞራልና የግብረ ገብ ይዞታ ይዘነጉ ይሆናል ብለው በመስጋት ፤

ለ/ ዲያቆናቱንና መነኰሳቱን በቅርብ በመቆጣጠር ሰፊ የሁለተኛ ደረጃን ትምህርት ቤት ለማስገባየት ።

ሐ/ የግእዝ ፤ የሃይማኖት ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ እንዲሰጥ በማሰብ አራት በዘመናዊ አቀድ የተሠሩ መማሪያ ክፍሎች ፤ አንድ የሳይንስ መማሪያ ላቦራቶ ርና አንድ ቤተ መጻሕፍት በሃያ ስምንት ሺህ ብር እንዲሠሩ ፕላን ተዘጋጀ ። ሥራው ከ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. በፊት ተጠናቀቀ ።




የሁለተኛው ደረጃ ት/ቤት ።

www.ethiopianorthodox.org

መማሪያ ክፍሎች ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የማስተማር ችሎታ ያላቸው ተጨማሪ ሦስት አሜሪካውያን መምህራን በቋሚ ሠራተኛነት ፤ ሁለት የዳች ተወላጆች ግማሽ ቀን የሚሠሩ መምህራን በድምሩ ከ፩ኛ እስከ ፲፩ኛ ክፍል መምህራን ተዘጋ ጅተው ቊጥራቸው ፳ ያህል ሲሆን፤ የት ምህርት መማሪያና የውስጥ ድርጅቱም በዚሁ ልክ ተሟልቶ ቀረበ ።

ቤት በተሟላ ይዞታ ደረጃው ከ፩ኛ—፲፩ ኛ ክፍል ከፍ ብሎ ጠቅላላ ፯፻፹ የሚሆኑ ተማሪዎችን መዝግቦ በማስተማር ላይ መሆኑን ታላቅ የምሥራች ያበሥራል ። በዚህም በሁለተኛው ደረጃ የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የአካዳሚክ ሥርዓተ ትም ህርት የተከተለ ሆኖ በተጨማሪ የግእዝ ፤



የሥላሴ ት/ቤት መምህራን በሙሉ ።

በተለይም የሳይንሱን ላቦራቶር መማ ሪያ ለማሟላት በተደረገው ከፍተኛ ጥረት በቂ ኬሚካሎችና የሳይንስ መማሪያ መሣሪያዎች በርዳታ መልክ ከቀዳማዊ ኃ. ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሊገኝ ተችሏል ።


ቤተ መጻሕፍት በማቋቋም በኩል በተ ደረገው ጥረት በግሽና በርዳታ በርካታ መጻሕፍት ተጠራቅመዋል ።

ስለዚህም በ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. የሥላሴ ት/


የሃይማኖት ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ፤ የፕሮጀክ ትና የማስተማር ዘዴ ትምህርት ይሰጣል ።

የትምህርት አሰጣጡም የተጣራና መም ህራኑ ለተማሪዎቹ ሰፊ ርዳታ እንዲሰ ስጡ ታስቦ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ተማ ሪዎች ቊጥር በየክፍሉ ከ፳፭ በላይ እንዳ ይሆን ሲወሰን በአንደኛ ደረጃም የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ስፋት ጋር ሲመ ዛዘን አነስተኛ መሆኑ ተረጋግጧል ።





የሁለተኛ ደረጃ ወንዶች ተማሪዎች ።



በሥላሴ ት/ቤት የሕፃናት ት/ቤት (መዋዕለ ሕፃናት ።

ከዚህም ሌላ ለሙከራ የኪንደር ጋር ደን ክፍል ተቋቁሟል ።

## የትምህርት ቤቱ ዓላማ ።

በዘመናዊና በመንፈሳዊ ትምህርት ቤታችን መልካም ምሳሌነት የሚታይባ ቸው ዜጎችን ለማትረፍ ሲሆን ለአንደ ኛው ያለው ተግባር ስለ የምእመናን ትብ ብርና ድጋፍ የሚያስፈልግ መሆኑን ትም ህርት ቤቱ ያምናል ።

የሥላሴ ት/ቤት ዲሬክተር

www.ethiopianorthodox.org

# ማኅበረ ክርስቶስ በአሥር ዓመታት ውስጥ

ሴቶች ልጆች በዘመናዊ ትምህርት ከወንዶች ጐን ተሰልፈው እኩል መማር የጀመሩበት ጊዜ ረጅም ባይሆንም ፡ በተለይ በቤተ ክርስቲያን በኩል ሁሉ ነገር በወንዶች ብቻ ተወስኖ መቆየቱ ግልጽ ነው ።

የሴቶችን ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መራቅ ምክንያት በማድረግ ማኅበረ ክርስቶስ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. በሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ አርቆ ተመልካችነት ከ፳ በማይበልጡ ወጣቶች በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥር ሊመሠረት ቻለ፤ በዚያን ጊዜ እንደዚህ ዓይነቱ ማኅበር በሀገራችን ውስጥ የመጀመሪያው ስለነበረ በሕዝቡ ዘንድ ብዙ ትችትና መገረምን አስከትሎ ነበር ። ቢሆንም «ሰው ካሰበው እግዚአብሔር የፈቀደው ይበልጣልና» በአምላክ ቸርነት በአንዳንድ ሰዎች አበረታችነትና ደጋፊነት እንዲሁም በልጆቹ መንፈስ ቆራጥነት ማኅበሩ ሥራውን ቀጠለ ።

ማኅበሩ ስሙ እንደሚያመለክተው በክርስቶስ የተመሠረተ ስለሆነ ዓላማው ክርስቲያናዊ ትምህርትን ተምሮ ማስተማር ፡ ሰብአዊ ርኅራኄን በክርስቲያናዊ ትምህርት መሠረት መፈጸም ፡ ክርስቲያናዊና ብሔራዊ ባህልን ለመጠበቅና ለማስከበር ፤ እንዲሁም ሴት ልጅ በማኅበራዊ ኑሮ ፡ በቤተ ክርስቲያንና በቤተሰብ በሚገባ አገልግሎትን መስጠት እንድትችል ለማድረግ ነው ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰጥዎን ለመቀበል የበቁት የማኅበረ ክርስቶስ አባሎች መሆናቸውን ማንም አይዘነጋውም ። ከዚህም በላይ የተለያዩ መዝሙሮችን በማጥናት ከቅዳሴ ሥነ ሥርዓት በኋላና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ጊዜ የደምብ ልብስ ለብሶ በመዘመር ፡ ለቤተ ክርስቲያን ድምቀትን የሰጡት የማኅበረ ክርስቶስ ፍሬዎች ናቸው ።

መዘምራቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በበዓላት ጊዜ ሥነ ሥርዓትን ለማስከበር ከካህናት ጋር ስለሚተባበሩ ፡ ከብዙ ተመልካች ምስጋና ደጋግሞ ደርሶአቸዋል ። ከሁሉ በበለጠ የማኅበሩ አባሎች የሚኮሩበት ነገር ቢኖር፤ለሌሎች ያሳዩት አርአያነት ነው ።



የማኅበረ ክርስቶስ መዘምራት ።

ይኸውም ማኅበረ ክርስቶስ ከመጀመሩ በፊት የእሱ ተመሳሳይ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር አልነበረም ። አሁን ግን በአዲስ አበባና በሌሎችም ብዙ ጠቅላይ ግዛቶች በየአድባራቱ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበሮች ይገኛሉ ። ትምህርትን ተምሮ ለሌሎች ካላካፈሉ «የጋን ውስጥ መብራት» መሆን ስለሆነ የማኅበሩ አባሎች «ተምሮ ማስተማር» በሚለው የማኅበሩ ዓላማ መሠረት ብዙዎቹ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበሮች ሲጀመሩ እየሔዱ በማስተማር ያላቸውን ዕውቀት አካፍለዋል ። ማኅበረ ክርስቶስ በዕድሜ ዝቅተኛ ለሆኑ ልጆች የእሑድ ት/ቤት በመክፈትና እናቶችንም በመሰብሰብ ትምህርት ለብዙ ጊዜ ለግሷል ።

ማኅበረ ክርስቶስ ሊስፋፋ የቻለው በማኅበረተኞቹ መሻሻል ነው ። ማኅበረተኞቹ እንዴት ሊሻሻሉ ቻሉ ? ይባል ይሆናል ። ማኅበረተኞቹ ሊሻሻሉ የቻሉት በትምህርት ደረጃ ከፍ በማለትና በአስተሳሰብ በመብሰል ነው ። በመንፈሳዊ በኩል የተመለከትነው እንደሁ ማኅበረተኞቹ ያላቸውን የመንፈሳዊ ትምህርት ጥማት በልዩ ልዩ ኮርሶች ተካፋይ በመሆን በመጠኑ ሊያረኩት ችለዋል ። ከአሁን በፊት ለሁለት ጊዜያት ያህል በካቴድራሉ መምህራን ተዘጋጅተውላቸው የነበሩትን የአራት ዓመታት ኮርሶች በመፈጸም ከግርማዊ ጃንሆይ እጅ የምስክር ወረቀት የተቀበሉት ወጣቶች ጥቂቶች አይደሉም ። ከዚህም በላይ ባለፈው ዓመት በርከት ያሉ የማኅበሩ አባ

www.ethiopianorthodox.org

ሎች የተምሮ ማስተማር ተግባራቸውን በቀለጠፈና በተጠና መንገድ ለማከናወን እንዲችሉ የሚረዳቸው ኮርስ ለሁለት ወራት ያህል ሰበታ በሚገኘው ገዳም ተካ ፍለዋል ።

የማኅበረ ክርስቶስ አባሎች በመንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ሳይወሰኑ፤በሥጋዊም ትምህርት ከሌሎቹ እኅቶቻቸውና ወንድሞቻቸው እኩል ይሰለፋሉ ። ባሁኑ ጊዜ ማኅበሩ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃዎች በሀገር ውስጥ ዩኒቨርስቲና በውጭ ሀገሮች ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚማሩና በልዩ ልዩ ኮርሶች የሚካፈሉ ፣ በተጨማሪም በሥራ ዓለም ላይ የተሠማሩ አባሎች አሉት ። የአባሎቹ በልዩ ልዩ ሙስክ መሰማራት በየአካባቢው የሚገኙትን ሌሎች እኅቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርቡ ለመገፋፋት አመችቷል።

በሥነ ጽሑፍም በኩል ማኅበሩ በሐዋርያዊ ድርጅት እየተዘጋጀ በወር አንድ ጊዜ በሚወጣው «ድምፀ ተዋሕዶ» ጋዜጣ ላይ «የሴቶችን ዓምድ» በመያዝ ሥነ ጽሑፍ ያቀርባል ። ከሁን በፊት « የሴት ልጅ ዕድገት በሃይማኖት» በሚል ርእስ ይታወቅ የነበረውን መጽሔት በየጊዜው ያወጣ ነበር ። ማኅበሩ በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ በሳምንት አንድ ቀን በተለይ ሴቶችን የሚመለከት ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን በማቅረብ የፕሮግራም ተካፋይ ነው ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ዘወትር እሑድ ከ፬ ሰዓት ተኩል እስከ ፮ ሰዓት ተኩል በሚደረገው የጸሎት ፕሮግራም ማኅበሩ ተካፋይ በመሆን በ፲፭ ቀን አንድ ጊዜ ኃላፊነት ወስዶ የጸሎቱን ክፍል ጊዜ ይመራል ።

ማኅበረ ክርስቶስ በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይወሰን በሀገር ውስጥ ካሉት ሌሎች ድርጅቶችም ጋር በመተባበር ይሠራል። ካሁን በፊት በተለያዩ ቦታዎች እየሔዱ መዝሙር በመዘመርና የተቸገሩትን ለመርዳት የተነሳው ድርጅቶችን ገንዘብ በመሰብሰብ ርዳታውን አበርክቷል ።

ማኅበሩ ወደፊትም ቢሆን እንዲህ ዓይነቱን ርዳታ ከመፈጸም አይቆጠብም ። ማኅበሩ ከኢትዮጵያም አልፎ በዓለም ከሚገኙ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ጋር በመጻጻፍ ግንኙነትን እየደረገ እንዲታወቅ ከመደረጉም በላይ ለማኅበሩ ጠቃሚ የሆኑ አሳቦችን በሥራ ላይ አውሏል ።

ከዚህም በላይ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገሮች ሴሚናር በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የሚወክሉ ልጆች እየሔዱ ተካፋይ ሆነዋል ። ለምሳሌ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. በአሜሪካ፣ በ፲፱፻፷፬ ዓ.ም. ደግሞ በዩጋንዳ በተደረገው ሴሚናር ላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በመወከል አንዲት የማኅበሩ አባል የሴሚናሩ ተካፋይ ሆናለች ። ሴሚናሩ በሀገር ውስጥ በሚዘጋጅበት ጊዜ ግን በርከት ያሉ እኅቶች በየጊዜው ይካፈላሉ

ማኅበረ ክርስቶስ ጠቅላላ የማኅበረተኞች ስብሰባ የሚያደርገው ዘወትር እሑድ ከሦስት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ተኩል ድረስ ነው ። ባሁኑ ጊዜ የማኅበረ ክርስቶስ አባሎች በሦስት ክፍል የተከፈሉ ናቸው ። በዕድሜ የተለያዩ ወጣቶች የተለያየ የማስተዋል ፣ የማመዛዘንና የአስተሳሰብ ችሎታ እንዳላቸው ስለሚታወቅና አባሎች ዕድሜያቸው የሚፈቅደውን ትምህርት ለማስተማር እንዲረዳ አከፋፈሉ የተመሠረተው በዕድሜ ነው ።



የመጀመሪያውና ዋናው ክፍል የተመደቡት ዕድሜያቸው ከ፲፬ ዓመት በላይ የሆነና በአስተሳሰብ በሰል ያሉ ወጣቶች ሲሆኑ ፤ በሁለተኛው ክፍል ያሉት ዕድሜያቸው ከ፯ እስከ ፲፬ ዓመት የሆኑ ናቸው። የሦስተኛው ክፍል አባሎች ደግሞ በዕድሜያቸው ከ፯ ዓመት በታች የሆኑ ናቸው ባሁኑ ጊዜ በአንደኛው ክፍል ፩፻፶ ልጆች፤ በሁለተኛው ክፍል ፺፩ ልጆችና በሦስተኛው ክፍል ፷፩ ልጆች በጠቅላላ ፪፻፸፫ አባሎች ይገኛሉ ። የትምህርት አሰጣፊልሞች የሚታዩበትና ማኅበረተኞቹ የእኅትማማች ውይይት የሚያደርጉበት ፕሮግራም አለ ። ጊዜ ሲያመችም የሽርሽር ፕሮግራም ይፈጸማል ። በሁለተኛውና በሦስተኛው ክፍል ያሉትም አባሎች ዕድሜያቸው የሚፈቅደውን ትምህርት ይማራሉ ፤ በአንደኛውና በሁለተኛው ክፍል ያሉት ወጣቶች ከአራት ተኩል እስከ አምስት ተኩል በቤተ ክርስቲያን የሚደረገውን የጸሎት ሥነ ሥርዓት ሲካፈሉ፤ ለሕፃናቱ ግን ይህ ሰዓት



የማኅበረ ክርስቶስ አባላት ።

ጡም ሁኔታ እንደየክፍሉ የተለያየ ነው በዋናው ክፍል የሚሰጡት ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ መምህራን መዘመር በአማርኛና በእንግሊዝኛ ፤ የመጀመሪያ ርዳታ የቤልትና ፤ የነር አመራር በዶ.ና የሃይማኖት ናቸው ። ከዚህም በላይ የተለያዩ ትምህርታዊ የመዝናኛና የመጫወቻ ጊዜ ይሆናል ።

ማኅበረ ክርስቶስ በአዳራሽ ለአባሎች ከሚያቀርበው ፕሮግራም በተጨማሪ ለሕዝብ በዓመት ከሦስት የበለጠ ጊዜ ዝግጅት ያቀርባል ። እነዚህም የክርክር የውይይት ፣ የቴያትርና የማኅበሩ ዓመታዊ ኤግዚቢሽን ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org



ማኅበረ ክርስቶስ ፲ኛ ዓመቱን ባከበረበት ወቅት ለኤግዚቢሽን ያቀረበው የእጅ ሥራ ።

ማኅበረ ክርስቶስን በበላይ ጠባቂነት የሚመሩት ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ሲሆኑ ፤ የማኅበሩን ልዩ ልዩ ፕሮግራም የሚያዘጋጁና ሥራ የሚያካሒዱ ሹማምንት በዓመት አንድ ጊዜ በአባሎች ይመረጣሉ ። በአባሎች የሚመረጡት ሹማምንት ፕሬዚዳንት ፤ ምክትል ፕሬዚዳንት ፤ ዋና ጸሐፊ ፤ ምክትል ጸሐፊ ፤ ዋና ገንዘብ ያዥ ፤ ምክትል ገንዘብ ያዥ ፤ የእጅ ሥራ ክፍል ኃላፊ ፤ የበጎ አድራጎት ክፍል ኃላፊ ፤ የድርሰት ክፍል ኃላፊ ፤ የንብረት ክፍል ኃላፊና የሽርሽር ኃላፊዎች ናቸው። በተጨማሪም በቋሚ አምስት የሆኑ መማክርት በሊቀ ሥልጣናት ሀ/ማርያም ወርቅነህ ይመረጣሉ ።

ማንኛውም ማኅበር ለሥራው ማከናወኛ ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ፤ ማኅበረ ክርስቶስም ምንም እንኳን መንፈሳዊ ቢሆን ዓላማውን ለማሳካትና ልዩ ልዩ ሥራዎችን ለመሥራት እንዲያመቸው የገቢ ምንጮች ይፈልጋል ። የማኅበሩ የገቢ ምንጮች ፤

ሀ/ ከአባሎች የሚገኝ የወር መዋጮ ፤

ለ/ በየጊዜው ከአባሎች እየተሠራ በዓመታዊ ኤግዚቢሽን የሚቀርበው የእጅ ሥራ ሽያጭ ገንዘብ ፤

ሐ/ ከልዩ ልዩ በጎ አድራጊዎች የሚሰጡ ስጦታዎች ፤

መ/ በካቴድራሉ ሥር ከሚካሔደው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ



ድርጅት በየወሩ የሚሰጠው የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ናቸው ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ምንጮች የሚገኘው ገንዘብ እስካሁን ድረስ ለዓመታዊ ኤግዚቢሽን ማዘጋጃ ፤ ለማኅበሩ ሥራ ማስኬጃ ፤ ለማኅበሩ ጽ/ቤት ቢሮ ማሠሪያ ፤ ለአላቂና ለነዋሪ ዕቃዎች መግዣና ለልዩ ልዩ ሥራዎች ማስፈጸሚያ ይውላል ።

ማኅበረ ክርስቶስ በበጎ አድራጎት ክፍል ኃላፊነት ከአንዳንድ በጎ አድራጊዎች ርዳታን በመጠየቅ ፤ ከአባሎች ልብሶችን በመሰብሰብ ሎተሪ እያዘጋጀ በመሸጥና ከአባሎች ልዩ ልዩ ርዳታዎችን በመጠየቅ ፤ የታረዙ ወገኖችን በማልበስ ይረዳል ። ከዚህም በላይ ከአባሎችም ውስጥ ችግረኛ ለሆኑት እኅቶች አንዳንድ ርዳታዎችን ያበረክታል ።

ማኅበሩ ዓላማው በጣም ሰፊ ሲሆን እስካሁን ድረስ ጊዜና ቦታ እንደፈቀደው የፈጸማቸው በከፊል ከላይ የተጠቀሱት ሲሆኑ ፤ ወደፊትም ከዚህ በበለጠ ለመሥራት ይጥራል ። ይህም እንዲሳካልን እምነታችንና ተስፋችን በክርስቶስ የጸና ነው ።

ማኅበረ ክርስቶስ

www.ethiopianorthodox.org